mastercard foundation

kifiya

ለአስቸኳይ ህትመት

# <u>ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ አነስተኛ የንግድ ተቋማት ላይ ከሚያስክትለው ጉዳት ለመታደግና ምርታቸውን ለማሳደግ የሚውል 3.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀቱን አስታወቀ</u>

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ሰኔ 2 ቀን 2012 ዓ.ም -** ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ ከሚገኙ 11 አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት ጋር በመተባበር የምርት ስራ ሂደታቸውን መልሶ ለማዋቀር እና በዚህም የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል የሚውሉ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን ማምረት እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል የትብብር ስምምነት ላይ መድረሱን አስታወቀ።

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን በአፍሪካ የሚገኙ ተቋማትን እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የኮቪድ-19 ወረርሽኝን የአጭር ጊዜ ተጽዕኖዎች ለመቋቋም እንዲችሉ እና በዘላቂነት የአደጋ መከላከል አቅማቸው እንዲጠናከር ለመደገፍ በተጀመረው የ<u>ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የኮቪድ-19 መቋቋሚያ መርሀ ግብር</u> በኩል 3.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅቱ አጠናቅቋል።

ይህ ለስድስት ወራት የሚቆይ የምርት ስራ መልሶ-ማዋቀር መርሀ ግብር 11 የሚሆኑ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት የንግድ ሰራቸው ሳይዘጋ እንዲቀጥል እና ከ1060 በላይ የሚሆኑ ሰራተኞች ከስራ ገበታቸው እንዳይፈናቀሉ የሚያደርግ ሲሆን ከእነዚህ ሰራተኞች መካከልም አብዛኞዎቹ ወጣት ሴቶች ናቸው። ይህ ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የሚገኘው ድጋፍ የፋብሪካዎች እና የአነስተኛ የጨርቃጨርቅ ማሽኖችን የምርት ሂደት መቀየር፣ እና ከዚህ ቀደም ተገዝተው ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሳሪያዎችን በመከራየት እና በመጠቀም የግል ደህንነት መጠበቂያ አልባሳትን ለህክምና ባለሙያዎች እንዲሁም የፊት መሸፈኛ ጭምብሎችን ደግሞ ለአጠቃላዩ ማህበረሰብ ለማምረት የሚውል ይሆናል። በዚህ የትብብር ድጋፍ ውስጥ የተካተቱት ድርጅቶች ኤንዚ ጫማ፣ ፊፍ ትደሬዲንግ፣ ጋበር ጨርቃጨርቅ፣ሀብቴ ጨርቃጨርቅ፣ካባና ሌዘር፣ ኩቴኬት ሌዘር፣ ማፊ፣ ሜሮን አዲስ አበባ፣ ሳዱላ የንግድ ስራ ኃ.የተ.የግ.ማ፣ ዘሉክ ኢንቲሪየር እና የፍቅር ናቸው።

በማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የኢትዮጵያ ዳይሬክተር አለማየሁ ኮንዴ ኮይራ እንደገለጹት "እንደአብዛኛዎቹ ታዳጊ ኢኮኖሚ ያላቸው ሀገራት ፣ በኢትዮጵያም ውስጥ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ቁጥር ያላቸውን ዜጎች በመቅጠር እና ምርቶቻቸውን ወደውጭ በመላክ ለሀገር ገቢ በማስገኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።በኮቪድ-19 ምክንያት የሚከሰተው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት ላይ በተለየ ሁኔታ ጉዳት የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ታዳጊ ኢኮኖሚዎችን በከፍተኛ

ሁኔታ የሚያሽመደምድ ነው። አነስተኛ ተቀማጭ ገንዘብ እና ውስን የመስሪያ ካፒታል ያላቸው  አብዛኛዎቹ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ

ተቋማት ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝን ለመቋቋም የሚቸገሩ በመሆኑ ይህ የትብብር ፕሮጀክት እጅግ አስፈላጊ ነው።"

በተጨማሪም አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት ኮቪድ-19 ያስከተለው ማህበራዊ መራራቅ በመደበኛ ሽያጫቸው ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ለመቋቋም እንዲችሉ እና በረዥም ጊዜ ያላቸው ጥንካሬ እንዲያድግ ለመርዳት  ምርቶቻቸውን በኢንተርኔት አማካይነት (በኢንተርኔት ወይም ኢ-ግብይት) እንዲሸጡ የሚያስችል ዕቅድንም ያካተተ ነው። በዚህ መሰረት ቀደም ብሎ የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን አጋር የሆነው ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂስ የፈንዱን አስተዳደር የሚመራ ሲሆን የኢንተርኔት ግብይት (ኢ-ግብይት) ድጋፍንም ያለምንም ክፍያ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ተቋማቱ የሚያቀርብ ይሆናል።

የክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ መስራች እና ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ሙኒር ዱሪ "ለአነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት የገንዘብ እና የገበያ ዕድል በማመቻቸት እንደ አስፈላጊነቱም በኢንተርኔት ግብይት፣ የዴሊቨሪ እና የዲጂታል ክፍያ ቴክኖሎጂዎች ድጋፍ በማድረግ ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር ያለንን አጋርነት ለማጠናከር በመቻላችን የላቀ ደስታ ይሰማናል። የማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ስትራቴጂ ሁሉን አቀፍ የሆነ እና ያሉትን ጊዜያዊ ችግሮች ለመፍታት ብሎም የወደፊት መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል መንገድ ነው። በመርሀ ግብሩ ውስጥ የታቀፉት አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማትም የንግድ ሰራቸውን መልሶ ለማዋቀር ከዚህ ጎን ለጎንም ያሉትን የዲጂታል አቅሞች ለመጠቀም በመቻላቸው የላቀ ደስታ ይሰማቸዋል፡፡" ሲሉ ገልጸዋል።

ይህ የአጋርነት መርሀ ግብር በአነስተኛ እና መካከለኛ ተቋማቱ መካል ጠንካራ የሆነ የትብብር መድረክን የፈጠረ ሲሆን ድርጅቶቹም ይህንን አስቸጋሪ ጊዜ በጥንካሬ ለመዝለቅ እና ከችግሩ ውስጥም ይበልጥ ጠንካራ ሆነው ለመውጣት ያስችላቸዋል።

"ይህ መርሀግብር ባይመጣ ኖሮ ድርጅታችንን ለመዝጋት እንገደድ ነበር። በኢትዮጵያ እንደሚገኙ አብዛኛዎቹ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማት፣ አብዛኛው ገቢያችን የሚገኘው ምርቶቻችንን ወደ ውጭ በመላክ እንደመሆኑ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በመጋቢት ወር አብዛኛው የኤክስፖርት ስራ ሲዘጋ በንግድ ስራችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ አሳርፏል። ከዚህ ባሻገርም የኮቪድ-19 ወረርሽኝን በመከላከል ስራ ውስጥ

ተሳታፊ ለመሆን በመቻላችን ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።" በማለት የካባና ሌዘር ዋና ስራ አስኪያጅ ሰምሀል ግዑሽ ገልጸዋል።

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን በአህጉራዊ ደረጃ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን የመከላከል ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ሰኔ 11 ቀን 2012 ዓ.ም ፋውንዴሽኑ ከአፍሪካ የበሽታ መከላከል እና ቁጥጥር ማዕከል(Africa CDC) ጋር የትብብር ስምምነት ማድረጉን አስታወቋል። በኮቪድ-19 መከላከል እና መቋቋም ፕሮግራሙ አማካይነት ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ለአፍሪካ የበሽታ መከላከል እና ቁጥጥር ማዕከል "Partnership to Accelerate Covi-19 Testing" ፕሮግራም ድጋፍ የሚውል 40 ሚሊዮን ዶላር መድቧል። ይህም ድጋፍ 1 ሚሊዮን የሚሆኑ የመመርመሪያ መሳሪያዎችን ለመግዛት እና ከ10 ሺህ በላይ የማህበረሰብ ጤና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን እና ለማሰማራት እንዲሁም የንክኪ ልየታ (Contact Tracing) የሚያከናውኑ 80 ፈጣን ምላሽ ሰጪ ቡድኖችን ለማቋቋም የሚውል ይሆናል። ከዚህ ባሻገር ድጋፉ ማዕከሉ በአህጉር ደረጃ ለወረርሺኙ የሚሰጠውን ምላሽ በተጠናከረ መልኩእንዲቆጣጠር የሚያስችል ይሆናል።

**ለተጨማሪ መረጃ**

---


**ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን**

ሔለን ዋይት፣ የፕሮግራም ኮሚዩኒኬሽንስ እስትራቴጂ ኃላፊ

ስልክ፡ +27 76 166 5372

ኢሜይል፡ hwhite@mastercardfdn.org

**ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ**

ስም፡ CPA ጆሹዋ ካምዌሬ

ስልክ፡ +251 904 312 836

ኢሜይል፡ jkamwere@kifiya.com

mastercard foundation

kifiya

## ስለ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን

ማስተርካርድፋውንዴሽን በአፍሪካ ያሉ ወጣቶችን እና በካናዳ የሚገኙ ነባር ማህበረሰቦችን ለመርዳት እና ለስብዕናቸው ክብር የሚሰጥ እና ዕርካታን የሚያጎናጽፍ የስራ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ ከተለያዩ ራዕይ ካላቸው ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል። ፋውንዴሽኑ በአለም ላይ ካሉ ታላላቅ የግል ፋውንዴሽኖች ውስጥ አንዱ ሲሆን ተልዕኮውም ትምህርትን ማስፋፋት እና የፋይናንስ አካታችነትን በማስፋፋት አካታች የሆነ እና ፍትሐዊ የሆነ አለም እንዲፈጠር መስራት ነው። ፋውንዴሽኑ በ2006 ዓ.ም የተመሰረተ ነጻ ተቋም ሲሆን የራሱ በሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና አስተዳደር የሚመራ ነው። ስለ ፋውንዴሽኑ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የተቋሙን ድረገጽ www.mastercardfdn.org ይጎብኙ።

## ስለ ክፍያ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂስ

ክፍያ የፊንቴክ ድርጅት ሲሆን የክፍያ፣ የስርጭት እና የዲጂታል አገልግሎቶችን የሚሰጥ እና ገንዘብ ነክ የሆኑ እና ያልሆኑ የንግድ ልውውጥ ስርዓቶችን ቀላል፣ አቅምን ባገናዘበ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ምቹ በሆነ ሁኔታ ለአነስተኛ እና ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች በማቅረብ ገበያቸውን የሚያስተዳደሩበትን፣ የሚሸጡበትን፣ ለደንበኞቻቸው አገልገሎት የሚያቀርቡበትን እና ከደንበኞቻቸው ጋር የሚገናኙበትን መንገድ በላቀ መልኩ እንዲያሻሽሉ የሚያስችሉ መንገዶችን የሚያመቻች ድርጅት ነው። ይህንን የምናሳካው ፈጠራ የፋይናንስ መሰረተ ልማቶችን እና ብቁ የሆኑ የስርጭት መንገዶችን በመጠቀም ፈጠራ የታከለባቸውን ቴክኖሎጂዎች በመገንባት ነው። የድርጅታችን አገልግሎቶች የደንበኞቻችንን እና የአጋሮቻችንን ወጪ የሚቀንሱ፣ ለገበያ ያላቸውን ተደራሽነት የሚያሳድጉ፣ ለካፒታል ያላቸውን ቅርበት የሚያሳድጉ እና ቀደም ሲል ያልተነኩ ዘርፎች ላይ እንዲደርሱ የሚያስችሉ ከመሆናቸውም በላይ የክፍያ አገልግሎቶችን ፍጥነት እና አቅም የሚጨምሩ ናቸው።

## ስለ አነስተኛ እና መካከለኛ የንግድ ተቋማቱ

**ኤንዚ ጫማ** የጫማ አምራች ድርጅት ሲሆን የአዲሱ አፍሪካዊ የፈጠራ፣ የጥበብ እና የንግድ ፍልስፍና ትርክት አካል ነው።

**ፊፍ ትሬዲንግ** ችግረኛ ሴቶች የተሻለ ክፍያ የሚያስገኙ ስራዎችን እንዲያገኙ የማሰልጠን እና ፋይዳ ኢን ፋሽን በተባለው ተቋሙ ውስጥ እንዲሰሩ ዕድል የመክፈት ተልዕኮ ያለው ድርጅት ነው።

mastercard foundation

kifiya

**ጋበር ጨርቃ ጨርቅ** በሀገር ውስጥ የተመረቱ ጨርቃ ጨርቆችን በመጠቀም በአለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ያለውን ስርጭት ለማሳደግ የሚሰራ እና **ሴቶችን ማጎልበት** የተሰኘ መሪ ቃል ያለው ድርጅት ነው።

**ሀብቴ ጨርቃጨርቅ** ከጨቅላ ህጻናት እስከ 14 ዓመት ታዳጊዎች ድረስ ላሉ ልጆች የሚሆኑ ልብሶችን የሚያመርት ሲሆን 77 በመቶ የሚሆኑት ሰራተኞቹ ሴቶች ናቸው።

**ካባና ሌዘር** ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የቆዳ ምርቶች የሚያርት እና ወደ ውጭ የሚልክ ድርጅት ሲሆን ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑ ሰራተኞቹም ሴቶች ናቸው።

**ኩቴኬት ሌዘር** ለሴቶች የተሻለ የስራ ዕድል በመፍጠር ትውልድ ተሻጋሪ ድህነትን ማቆም ይቻላል የሚል ዕምነት ባላቸው ሁለት ኢትዮጵያውያን ስራ ፈጣሪዎች የተቋቋመ ሲሆን ከሰራተኞቹ ውስጥ 95 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።

**ማፊ** የዕጅ ጥበብ ሙያን፣ ሴቶችን ማጎልበትን እና ወቅቱን የጠበቀ ፋሽንን ያዋሀደ እና ምርቶቹን በኢትዮጵያ በማምረት ሴት የእጅ ጥበብ ባለሙያዎችን የሚደግፍ ድርጅት ነው።

**ሜሮን አዲስ አበባ** የቆዳ ምርቶችን በመንደፍ፣ በማምረት እና በማሰራጨት ላይ የተሰማራ ሲሆን ቦርሳዎችን፣ የተለያዩ መጠቀሚያዎችን፣ ጃኬቶችን እና ጫማዎችን ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ሀገራት ያቀርባል።

**ሳዱላ ንግድ ኃ.የተ.የግ.ማ** ላሊ እና ዝናር በተሰኙ ሁለት ብራንዶቹ አማካይነት ለባህላዊ ሸማ ሰሪዎች ነጻ ስልጠና በመስጠት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ስራቸውን እንዲያከናውኑ እና የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ብሎም ዕውቀታቸውን ለአዲሱ ትውልድ እንዲያስተላልፉ የሚሰራ ድርጅት ነው።

**ዘ ሉክ ኢንቲሪየር** በኢትዮጵያውያን የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች በተሰሩ የቤት ውስጥ መጠቀሚያዎች የቤት ውስጥ ማሳመሪያዎችን በማከናወን በማህበረሰቡ ውስጥ በጎ ተጽዕኖን ለመፍጠር የሚሰራ ድርጅት ነው።

**የፍቅር** የፋሽን ዲዛይን ድርጅት ሲሆን በኢትዮጵያ ፋሽን እና የአልባሳት ገበያ ውስጥ ያሉትን ዕድሎች የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን በመጠቀም ለማስተዋወቅ የሚሰራ ድርጅት ነው።